በ 2020 የተሻሻለው የ ኤል ጂ ቢ ቲ ኪው (LGBTQ) አዛውንቶች እና ኤች አይ ቪ (HIV) ያለባቸው አዛውንቶች እንክብካቤ ማሻሻያ ሕግ የዲሲ የሰብዓዊ መብቶች (DC Human Rights Act) ህግ መስርያ ቤት ከአድልዎ ነጻ ስለመሆን የተሰጠ ማስታወሻ

ሚያዝያ (April) 21 2026

በዲስትሪክት አፍ ኮሎምቢያ በሚደረጉ ጥበቃዎች (District of Columbia Protections within Long-Term Care Facilities) ስር በረጂም ግዜያት እንክብካቤ ተቋሞች ውስጥ ስላሎት መብቶች ይወቁ።

1. የዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ (DC Human Rights Act) - በ 2020 የተሻሻለው የ ኤል ጂ ቢ ቲ ኪው (LGBTQ) አዛውንቶች እና ኤች አይ ቪ (HIV) ያለባቸው አዛውንቶች እንክብካቤ ማሻሻያ ሕግ

በ 1977 የወጣው የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ (DCHRA)፤ በኤል ጂ ቢ ቲ ኪው (LGBTQ) አዛውንቶችና ኤች አይ ቪ (HIV) ባለባቸው አዛውንቶች ሕግ እንደተሻሻለው፤ የረጂም ግዜያት እንክብካቤ በሚሰጡ ተቋሞች ውስጥ ያሉ ግለሰቦች፡ በ 1) ጾታዊ አመለካከት 2) ጾታዊ ማንነት ወይም አገላለጽ ወይ 3) በኤች አይ ቪ (HIV) መያዝ ምክን ያት እድልዎ እንዳይደረግባቸው ይጠብቃቸዋል።

2. የረጅም ግዜ እንክብካቤ በሚያደርጉ ተቋሞች የሚከለከሉ

የረጂም ግዜ እንክብካቤ ሰጪ ተቋሞች፣ ሰራተኞቻቸው እና ከእነሱ ጋር ኮንትራት ያላቸው ሰዎች፤ በግምት በሚመስላቸው አስተያየትም ሆነ ሆነ ትክክል በሆኑ የግለሰቦች ጾታዊ አመለካከት፣ ጾታዊ ማንነት ወይም አስተያየት ወይም ባላቸው የኤች አይ ቪ (HIV) ችግር በመነሳት ከታች የሰፈሩትን ማንኛቸውንም እርምጃዎች ለመውሰድ የተከለከሉ ናቸው፤

1. ማንኛውንም ግለሰብ የረጂም ግዜ እንክብካቤ በሚያደርጉ ተቋሞች ውስጥ እንዳይገባ መከልከል
2. አንዱን ኗሪ ከአንድ ተቋም ወደሌላኛው ተቋም እንዳይዛወር መከለከል ወይም በግድ እንዲዛወር ማድረግ
3. አንዱን ኗሪ ማስወጣት ወይም ማባረር
4. አንድ ኗሪ ከሌላ ተቀማጭ ጋር ክፍል ለመጋራት ሲፈልግ መከልከል
5. ተቀማጩ ሰው ካልጠየቀ በስተቀረ፤ አንዱን ጾታውን የቀየረ ሰው በጾታ አመለካከቱም ሆነ ማንነቱ ከማይስማማው ሰው ጋር በአንድ ክፍል መመደብ
6. አንድን ሰው መታጠቢያ ቤት ወይም ሌሎች ከጾታው ጋር የሚቀናጁ ተቋሞችን ለመጠቀም ሲፈልግ የግል መታወቅያ ወረቀት እንዲያሳይ ውይም ሌላ ማረጋገጫ

እንዲያቀርብ መጠየቅ

7. ስለ ምርጫቸው ግልጽ ማብራርያ ከተሰጣቸውም በኋላ ተቀማጩ ሰው ሊጠቀምበት የመረጠውን ስም ወይም ተውላጠስም ሆን ብሎ በእውቅ አለመጠቀም

8. በጾታዊ ማንነታቸው ወይም በጾታዊ አመለካከታቸው ምክንያት ተቀማጮች ያፈልጉትን ልብስ የመልበስ ፤ ጌጣጌጥ ወይም ሜክ አፕ (ማቆነጃጀያ) የማድረግ መብት መከልከል

9. አንድ ተቀማጭ ያለውን የግላዊነት መብት ወይም ከሌሎች ተቀማጮች ወይም ጎብኚዎች ጋር ያለውን የመገናኘት፣ ጾታዊ ግኙነቶችንም የማድረግ መብትን መከልከል ወይም

10. ተቀማጮችን ተገቢ የሆነ የሕክምና እንክብካቤ ወይም ሕክምናን የማይመለከት ሌላ እንክብካቤ እንዳያገኙ መከልከል ወይም መገደብ ወይም ምክንያታዊ ባልሆነ መንገድ ክብራቸውን የሚነካ ወይም በቀላሉ መወገድ የሚችሉ ምቹ ያልሆኑ ነገሮች እንዲከሰቱ ማድረግ

የረጂም ግዜ እንክብካቤ የሚያደርጉ ተቋሞች፣ ሰራተኞቻቸውና ከእነሱ ጋር በኮንትራት መልክ የሚሰሩ ሁሉ ተቀማጮችን የማስገደድ፣ የማስፈራራት፣ ቂም በቀል የመወጣት ወይም በምንም ዓይነት መንገድ በዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ሕግ (D.C. Human Rights Act) የተጠበቁትን የግለሰብ መብቶችን መጣስ የተከለከለ ነው።

3. የተቀማጮች ግላዊነትና የእንክብካቤ ጥበቃን በተመለከተ

- ተቀማጮች ራሳቸው ፈቃዳቸውን ካልሰጡ በስተቀረ፤ ልብሳቸውን በከፊል አውጥተው አካላዊ ምርመራ ሲደረግላቸውም ሆነ ሌላ የግል እንክብካቤ በሚደረግላቸው ወቅት፤ ቀጥታዊ እንክብካቤ በመስጠት በኩል የማይሳተፉ ሰራተኞች ወይም ባለ ኮንትራቶች በምርመራው ክፍል ውስጥ መገኘት አይፈቀድላቸውም።

- ተቀማጮቹ፤ ልብሳቸውን በከፊልም ሆነ በሙሉ አውጥተው ምርመራ በሚያደርጉበት ወቅት ከሌላ ሰው እይታ የሚያግዳቸው በር ወይም መጋረጃ ወይም ማንኛውም ዓይነት ሽፋን ተቋሞቹ ማድረግ አለባቸው። ሊደርግላቸው ይገባል።

- ተቀማጮች ወይም ወኪሎቻቸው፤ ስለአሏቸው መብቶች ገለጻ የማግኘት መብት አላቸው፤ እንዲሁም የመጀመርያው ዓላማ በሽታ ለመከላከል ወይም ጤንነትን ለመጠበቅ ሳይሆን ትምህርታዊ ወይም መረጃ ለመስጠት እስከሆነ ድረስ ማንኛውንም ምርመራ፣ ክትትል ወይም ሕክምና አልፈልግም የማለት መብት አላቸው። ይህ ደግሞ የበሽተኛውን የመመርመር ወይም ሕክምና የማግኘት ዕድሉን የሚያጎድል ወይም የሚቀንስ መሆን የለበትም።

4. የግል መረጃን በተመለከተ የሚደረግ ጥበቃ

- ተቀማጩ የረጅም ግዜያት እንክብካቤ ለማግኘት ወደ እነዚህ የረጂም ግዜያት እንክብካቤ ተቋሞች ውስጥ ለመግባት ገና ሲመዘገብ፤ ስለጾታዊ ማንነቱ፤ ጾታዊ አመለካከቱ እንዲሁም መጠራት ስለሚፈልግበት ስም እና ተውላጠ ስም መረጃ የመስጠት ምርጫ ይሰጠዋል።

- በፌደራላዊው መንግስትና በዲስትሪክቱ ሕግ መሰረት፤ እነኚህ የረጂም ግዜያት እንክብካቤ የሚያደርጉ ተቋሞች የተቀማጮችን ጾታዊ አመለካከት፣ ጾታዊ ማንነት፤ የሽግግር ታሪክ እና የኤች አይ ቪ (HIV) ሁኔታን በተመለከተ ስልጣን ከሌላቸው ሰዎች ወይም አካላት በሚስጢር ይይዛሉ።

- እነኚህ የረጂም ግዜያት እንክብካቤ ተቋሞች፤ የተቀማጮችን ጾታዊ አመለካከት፣ ጾታዊ ማንነት፤ የሽግግር ታሪክ እና የኤች አይ ቪ (HIV) ሁኔታን በስህተት ወይም ባለማወቅ ለሌሎች ተቀማጮች፣ ጎብኚዎች ወይም ኮንትራክተሮች ይፋ የመውጣት ዕድልን ለማጥበብ ምክንያታዊ የሆኑ እርምጃዎችን ይወስዳሉ።

5. ጥሰት ሲያጋጠም አቤቱታ ማቅረብን በተመለከተ

አንድ የረጂም ግዜያት እንክብካቤ የሚሰጥ ተቋም የዚህን ሕግ ክፍል ጥሷል የሚል እምነት ካሎት፤ ጉዳዩ በተፈጸመ በአንድ ዓመት ውስጥ፤ ህግ ወደሚከበርበት ፍርድ ቤት ወይም ወደ ዲሲ የሰብዓዊ መብቶች መስርያ ቤት (DC Office of Human Rights (አ ኤች አር OHR) አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። ወደ አ ኤች አር (OHR) አቤቱታ ማቅረብ ነጻ ነው፣ ገንዘብ አይከፈልበትም። ይህንንም አቤቱታ ለማቅረብ ጠበቃ ማድረግ አስፈላጊ አይደለም። ወደ አ ኤች አር (OHR) አቤቱታ ለማቅረብ የአዛውንት እንክብካቤ የአቤቱታ ፎርም(Care for Seniors Complaint Form) ሞልተው በሚከተለው መንገድ ማስገባት ይችላሉ፡

- በአንላይን https://s.dc.gov/FileDiscriminationComplaint ይጎብኙ።

- በኢሜል፡ ohr.intake@dc.gov ይጻፉ።

- በፖስታ ወይም በአካል፡ 441 4th Street NW, Suite 570N, Washington, DC 20001 በፖስታ ይጻፉ ወይም በአካል ይሂዱ

- ፋክስ፡ (202) 727-9589

በአ ኤች አር ((OHR) ውስጥ ስለሚካሄደው ሂደት ላሎት ጥያቄዎች በስልክ ቁጥር(202) 727-4559 በመደወል መልስ ማግኘት ይችላሉ።

ለተጨማሪ የፕሮግራም እርዳታ ወይም በኦ ኤች አር (OHR) ውስጥ ስለሚገኘው የአዛውንት እንክብካቤ ፕሮግራም (Care for Seniors Program)ን በተመለከተ መረጃ ከፈለጉ ከፕሮግራሙ ሰዎች ጋር ይገናኙ፤

- ኢሜል፡ careforseniors.ohr@dc.gov
- የስልክ ቁጥር፡ (202) 481-3773